# ስንቴ መሞኘት ይኖርብናል?

**ከእሳቱ አሸናፊ**

ካላነሰ በስተቀር ግማሽ ሚሊዮን ዜጋ በመንግስቱ ሃይለማሪያም የፋሽስት መንግስት በግፍ ተገድሏል። የታሪክ ሃቅ ነውና ፋሽቱ መንግስት የሞት ሽረት ትግል ያደረገው የሕዝብ ወገን ከሆነው ኢሕአፓ ጋር ነበር። ደርግ ያለ ኢሒአፓ እንዲሁም ኢሕአፓ ያለ ደርግ ታሪካቸውን ለማውራት አይቻላቸውም። የሚያሳዝነው ግን የደርግን ጀግንነት የሚያወጉን ጸሃፊዎች መሬት አንቀጥቅጡን የኢሕአፓ ታሪክ እንዳልነበር ያልፉታል። ጸሃፊዎቹ የደርግ አፍቃሪዎች ወይም በትክክለኛ አገላልጽ ራሰቸው የግፍ ደም በጃቸው ላይ ያለባቸውና ታሪካቸውን አዳሽ ጸሃፊዎች መሆናቸው ነው። ድንቄም። ታሪክ የጥሩና የመጥፎ ድርጊቶች ጥርቅም ነው። የደርግን ጥሩነት ለመናገር በወቅቱ አስጨናቂ የነበረው ባላንጣውን ኢሕአፓ መጥፎነት (ኢሕአፓ መጥፎነት ካለው) ከነማረጋገጭውቅ ማቅረብ ይገባል።

የደርግ የምርመራ ዘዴ በጣም የከፋና የጨካኝ አገሮችን ተመክሮዎች በሙሉ ያካበተ ነበር። ወያኔ ገልብጦ ገረፈኝ ሲባል መስማቱ ማሳዘኑ ይጠበቃል። ግርፋት ወይም ስየል የጨካኝ መንግስታት መሳሪያ ነው አሜሪካንን ጨምሮ። የዛሬዎቹ ፓለቲከኞች የወያኔ ስየል ከደርጉ ስየል የከፋ ነው ለማለት ሲዳዱ ደርጎቹ ደግሞ ወያኔ አለም ያላየው አዲስ ስየል አለው ይሉናል። ለነገሩ መርፌም የሰረቀና መ,ኪና የሰረቀ ሁለቱም የሚባሉት ሌባ አይደለ? አንድ የገደለና መቶ የገደለ ያው ገዳይ ነው የሚባለው። ደርግም ወያኔም ገዳይ ፋሺስቶች ናቸው። የደርግን ግፍ በመናገር የወያኔን ግፍ ለማሳነስ መሞከር ስየልና ሞት በተቀበለው ሃገር ወዳድ ወገን ላይ ክህደት መፈጸም ነው።

ደርግ ውስጥ የነበረ ካድሬ ያውም ስንት ነብስ አጥፍቶ ዛሬ ከተቃዋሚ ድርጅት አባል ሆኖ ወያኔን መታገሉ ከደሙ ንጹህ ያደርገኛል ብሎ ካሰበ እንደ  የግንቦቴው ታጋይ ሞኝ ሆኗል ማለት ንው። የቀይ ሽብር ዋነኛዎቹ ግንባር ቀደሞቹ ባብዛኛው መሸሸጊያቸው የእምነት ቤቶች ሁነዋል። የዕምነት ቤቶቹም ወይ በሞኝነት አለያም እኔም እንደርሱ ነበርኩ በማለት ማስተናገታቸው አንድ ቀን ጠያቂ ሊነሳባቸው እንደሚችል ማወቅ አለባቸው አሽልቧልቸው ከሆነ።  ቀኝ ፊቴን ያደበነኝን ባላንጣዬን ለምን መጽሃፋቸው ግራህን ስጥው የሚለኝ? መባል መሆን የነበረበት ከመታሃ አንተም አጡዘው ማለት አልነበር?

ቀይ ሽብር፣ ነጭ ሽብር፣ አረንጓዴ ሽብር፣ ብጫ ሽብር . . .  ምናልባትም ጥቁር ሽብር ይባል ሽብር ሽብር ነው። ቀለሙ ጥሩ ወይም ክፉ ሽብር ብሎ አይለየውም። ሞት ሞት ነው፣ ስየል ስየል ነው፡ ግርፋት ግርፋት ነው። ሽብርም ሽብር ከመሆን የሚያመልጥበት ከሂትለር እስከ መንግስቱ ታሪክ ድረስ የተሰጠ ሳይንሳዊ መረጃ አልቀረበም። መንግስቱም ገደሏል፣ ወያኔም ረፍርፏል። አንዱን ጥሩ ገዳይ ሌላውን መጥፎ ገዳይ አድርጎ ሊያቀርብልን የሚፈልግ ተላላ ወይም ተቀጣሪ ከመደከም የተሻገረ ውጤት አይኖራቸውም።

አንድ ኮሮኔል ደርግን ሸሽቶ ስንት ድራማ ከሰራብን በኃላ ወደ እምነት ቤት ገባ፡፡ ታምራት ላይኔ ከኢሕአፓ ከድቶ ወያኔ ሆኖ ኢሕኢፓዎችን በግፍ ረፍርፎ የወያኔ ሁለተኛ ሰው እስከመሆን ደረሰና ወደ መጨውረሻ ስቻር ሰረቀ ተብሎ ከርቸሌ ገባ። ሲፈታ ወደ እምነት ቤት ተጠለለ። ተደበቀ። ወደፊት የዕምነት ቤቱን አውግዞ ለመክዳት እንደሚሞክር ትንቢት መናገር የምችል ይመስለኛልና ሲሆን አትደነቁ። በዚያ ኦርቶዶክስና ጴንጤ ቤተ እምሽነት ስንት ገዳዮች እንደተሸሸጉ እንደምናውቅ ይጠራጠሩ ይሆን? ለነገሩ እኮ ቤተ እምነት ከጻድቃን ይልቅ ወንጀለኞችን ወይም ሃጢያተኞችን መሰብሰብና ማስተማር ነው ተግባሯ ይባላል። አንዳንዴ ለቤተ እምነት የማይስማማ አመለካከት አለኝ። የአሜሪካን ጥቁሮች ባሪያ በመሆን ከከብት አንስወፉ እንደ እቃ ተቆጥረው ለዘመናት ሲሰቃዮ በየመንደሩ ከመኖሪያ ቤት ያልተናነሰ ቁጥር ያላቸው የቤተ እምነቶች ምነው ግፉን አላወገዙም? ሞሰሎኒ ኢትዮጵያን ለመውጋት ሲነሳ ተገቢ አይደለም በማለት ለምን የካቶሊክ ቤተ እምነት ተቃውሞ አላቀረቡም? የኢትዮጵያ የእስላሙና የክርስቲያኑ እምነት ቤት ለመሆኑ ጭራቅ ገዢዎችን - ሃይለስላሴ፣ ደርግና ወያኔን- እባካችሁን ሕዝቡን አትርገጡ ብለው ነበርን? በዚያ ቀይ ሽብር ወቅት መንግስትን ገዝተው ነበርን?

የደርግን ቀይ ሽበር የወያኔ የብሄርተኝነት ሽበር፣ የሃይለስላሴን ንጉሳዊ ሽብር ማበላለጡ ምን ጥቅም አለው? ከሃይለስላሴ የማይሻል የለም ተብሎ ጭራቁን የመንግስቱን ፋሺዝም ተሰይሞብን ከግማሽ ሚሊዮን ብርቅዬ ኢትዮጵያውያንን አልበላም? ከደርግ የማይሻል የለም ተብለን ጎርደንዲኖስ የሆነ የሰው ሰይጣን ወያኔን ታቅፈን መውጫው ጠፍቶን በመታመሰ ላይ አይደለንም? ዛሬ የሚወራልን ያንዱን ግፍ ካንዱ ግፍ ከማስበለጥና ከማሳነስ ላይ ሆኗል። አንዱ በጩቤ ይገድላል። ሌላው በማሽንገን ይገድላል። ይህኛው ደግሞ በመርዝ ይገላል። ሁሉም የሚጠሉትን በሰራላቸው ዘዴ ይገድላሉ። ውጤቱ ግድያ ነው። ይሄኛው የመግደያ ዘዴ ከዚያኛው ይሻላል ብለው ከሚሰብኩ ፓለቲካኞች ዘመን ላይ ደርሰና። ሰሞኑን ወያኔ ስየል አደረሰብኝ የሚል ሰው በየሚዲያው ሲወራለትና ሲያወራ አዳምጫለሁ። እኔም ያለፍኩበት በመሆኑ ለዘንደሮው ተጠቂ ክልቤ አዝኛለሁ። ተገልብጦ የውስጥ እግርን መገረፍ፣ በብልት ላይ ጠርሙስ ማንጠለጠል . . . . በቆዳ ላይ የሚንጠባጠብ የሳስቲክ እሳት፣ በኤሊክትሪክ መጠበስ፣ በጉጠት የጣት ጥፍሮችን መንቅል . . . . የቱን መምረጥ ይሻላል????? የደርግ ስየል ከወያኔ ስየል የተሻለ ነው የሚል መልዕክት ከተጠቃው ሰው ሳይሆን ታሪኩ ክሚናገሩለት ሰው መሰማት ተጀምሯል።

የዚያን ትውልድ ግፍ በወቅቱ ለመግለጽ ዘዴዎቹ አመቺ አልነበሩም። የዛሬውን ለማዳረስ እድሜ ለሶሻል ሚድያ ባንድ ጊዜ በተደጋጋሚ በትክክልም ሆነ አወላነ ማቅረብ ይቻላል። ያውም ዜና አቅራቢዎቹ በደርግ ዘመን ስየል የፈጸሙ ሆነው። ልብ ማለት ያለብን የኔ ስየል ካንተ ስየል ይብሳል ወይም ከደርግ ስየል የወያኔ ይከፋ ነው ክርክር ውስጥ መግባቱ ጉንጭን ካማድከምና አፍ ምግብ በቅጡ እንዳይበላ ከመበደል የተሻለ የሚያመጣው ውጤት የለውም። የወቅቱን የሕዝብ ጠላት ከወገቡ ላይ ለማውረድም የቅንጣት ያህል አስተዋጾኣ ኣያመጣም። መሆን ያለበት በግፍ ስየለ የተቀበሉትን ወገኖቻችንን ምሳሌነት ተከትለን አሁን ያለውን ጠላት ወያኔን ድባቅ ለመምታት መራመድ ነው። ማዘን ሳይሆን ማመጽ ነው የሚገባን።

ወያኔን አሜሪካን ሆኖ መኮነን ይቻላል። አስመራም ሆኖ መሳደብ ይቻላል። ከአሜሪካ የጥጥቅ ትግል ወደ ኤትዮጵያ የማስገባት ሕልም ብዙ ችግር አለው። በመጀመሪያ ታጣቂ ማግኘቱ ህልም ነው። ለዚህ አይነቱ ትግል መደራጀቱ ደግሞ ከሕግ ውጭ ነው። የአስመራው ግሕ የሌለበት አገር በመሆኑ አመቺ ነው ጀግና ከተወለደ። ግን የሞራሉና የፍትህ ጥያቄ እንዴት ይታረቃል? ወያኔ ግፈኛ፣ ጸረ ዲሞክራሲ፣ ጸረ ሕዝብ . . . .ነው እየተባለ እንዲያውም ሃቁ በቀን ከመቶ በላይ ወጣቶች የጭንቅ ሆኖባቸው ወደ ወያኔ ግዛት ሲሸሹና ወደ አራት ሺህ ወጣት በየወሩ ከኤርትራ እየሸፁ በአውሬ፣ በበረሃና በየውቅፍያኖሱ እየሰመጠ ሲያልቁ ኤርትራን ተገን አድርጎ የሚታሰብ ትግል ምንኛ ፍትህ አለው? ለኔ ከኤርትራ የሚጅመር ትግል ባፍንጫዬ ይውጣ። ለኔ ወያኔም ሆነ ከኤርትራ ምድር ኢትዮጵያን ነጻ እናወጣልን የሚሉ የአርበኖችን ስም የየዙ ወይም የወር ስም የያዙ ድርጅቶች በሙሉ ሳይፈጠሩ የሞቱ ናቸው። ላለውም ትግል መሰናክል ናቸውና አንቅረን መትፋት አለብን። ተጠያቂ የሚሆኑት እነዚህ ድርጅቶች ብቻ ሳይሆኑ ገንዘቡ የሚያፈስላቸውም በሙሉ ናቸው። ልብ በሉ ኢትዮጵያ ታሪከኛ አገር ናት። ጠላቷንና ወዳጇን የምትጠይቅበት ጊዜ ከነገ የቀረበ ነውና።

ማጠቃለያው መፍትሄው ቀይ፣ አረንጓዴ፣ ብጫ፣ ወይም ነጭ ሽብር እያሉ የነበረውን የግፍ ሽብር ማድበስበስ አይጠበቅብንም። ታሪክ በምንም መንገድ ሃቅን ከማውራት አትደክናምም። የወያኔ ግርፋት ከደርግ ይበልጣል አተካሮ ውስጥ በመግባት ከትግሉ አንፋዘዝ። መጠለያችን፤ መሸሸጊያችን፣ ዋሻችንና ጫካችን ኢትዮጵያና ሕዝቧ እንጂ ኢሳያስ አለመሆኑ ለነዚያ ባተሌ ተላላ ሞኝ ድርጅት ነን ባዮች ደፍረን ካመናገርና ላሜ ቦራ ሆነን ገንዘባችንን በመለገስ በገዛ እናት አግራችን ላይ ጦር አንምዘዝ። ወያኔን አውርደን ኢሳያስን ዳግመኛ እንዳነነግሰው መንቃት ይገባናል።